የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፷፩
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No. 61
ADDIS ABABA 4th September, 2012


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፩/፪ሺ፬ ዓ.ም

የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል አዋጅ ……ገጽ ፮ሺ፭፻፵፯


CONTENTS


Proclamation No. 761/2012

Telecom Fraud Offence Proclamation …. Page 6547


## አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፩/፪ሺ፬

## ስለቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል የወጣ አዋጅ

በየጊዜው እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ያለው የቴሌኮም ማጭበርበር ተግባር የቴሌኮም ኢንዱስትሪው ለሀገሪቱ ሰላም፣ ልማትና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ መጫወት የሚገባውን ቁልፍ ሚና እንዳይጫወት ፈተና እየሆነ መምጣቱን በመገንዘብ፤

የቴሌኮም ማጭበርበር ከሚያስከትለው ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ባሻገር የሀገሪቱን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ስጋት መሆኑን በመረዳት፤

በስራ ላይ ያሉት የሀገሪቱ ህጐች በበቂ ሁኔታ በቴሌኮም ኢንዱስትሪው ላይ እየደረሱ ያሉትን ጥቃቶች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ባለመሆናቸው የተሟላ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል አዋጅ ቁ□ር ፯፻፷፩/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION No. 761/2012.

## A PROCLAMATION ON TELECOM FRAUD OFFENCE

WHEREAS, considering that telecom fraud is increasing and wide-spreading from time to time thereby encumbering the telecom industry to play an essential role in the implementation of peace, democratization and development programs of the country;

WHEREAS, recognizing that telecom fraud is a serious threat to the national security beyond economic losses;

WHEREAS, it has became imperative to legislate adequate legal provisions since the laws presently in force in the country are not sufficient to prevent and control telecom fraud;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Telecom Fraud Offence Proclamation No. 761/2012".

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

፩/ "የቴሌኮም አገልግሎት" ማለት የቴሌኮም ማዞሪያዎች አገልግሎት፣ ሴሉላር ሞባይል አገልግሎት፣ የኢንተርኔት አገልግሎት፣ የሳተላይት ቴሌፎን አገልግሎት፣ የዳታ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ የቴሌ ሴንተር አገልግሎት ወይም ሪሴል አገልግሎት፣ የተንቀሳቃሽ ወይም የቋሚ የሬድዮ አገልግሎት፣ የቪሳት አገልግሎት፣ የኬብል ዝርጋታና ጥገና ስራ፣ የቴሌኮም ማዞሪያዎች ተከላና ጥገና ስራ፣ በኤሌክትሪክ ወይም በኤሌክትሮ ማግኔቲክ ኃይል አማካኝነት በስልክ ሽቦ፣ በሬድዮ፣ በሳተላይት፣ በኦፕቲካል ፋይበር ወይም በሌላ ኤሌክትሮ ማግኔቲክ ወይም ማናቸውም ሌላ ስልት ድምፅ፣ ምልክት፣ ፅሁፍ ወይም ምስል ማሰራጨት ወይም መቀበል እንዲሁም ሚኒስቴሩ የቴሌኮም አገልግሎት ብሎ የሚወስናቸውን የሚጨምር ሲሆን የብሮድካስቲንግና የኢንተርኮም ግንኙነትን አይጨምርም፤

፪/ "የቴሌኮም መሳሪያ" ማለት ለቴሌኮም አገልግሎት የዋለ ወይም ሊውል የታቀደ ማንኛውም መሳሪያ ሲሆን የመሳሪያውን ተገጣሚ አካልንና ሶፍትዌርን ይጨምራል፤

፫/ "የኮል ባክ አገልግሎት" ማለት የሀገር ውስጥ የቴሌኮም ድርጅት ሳያውቀው የሌላ ሀገር የቴሌኮም ድርጅት ጥሪ ቶንን ለዓለም አቀፍ ግንኙነት መጠቀም ወይም ዓለም ዓቀፍ የስልክ ጥሪዎችን የሀገር ውስጥ ማስመሰል ሲሆን በዓለም ዓቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን ህብረት ኮልባክ ተብለው የሚታወቁአገልግሎቶችንም ይጨምራል፤

፬/ "ሚኒስቴር" ማለት የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነው፤

፭/ "የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪ ድርጅት" ማለት ኢትዮ-ቴሌኮም ወይም የቴሌኮም አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሌላ ሰው ነው፤

፮/ "ፖሊስ" ማለት የፌዴራል ፖሊስ ወይም እንደሁኔታው የክልል ፖሊስ ነው፤

፯/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

## 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ ‘‘telecom service” means public switched telecom service, cellular mobile service, internet service, satellite telephone service, data communication service, telecom-centers or resale service, mobile or fixed private radio service, very small aperture terminal (VSAT) service, cable installation and maintenance service, telecom switches installation and maintenance service, the transmission or reception through the agency of electricity or electromagnetism of any sounds, signs, signals, writing, images or intelligence of any nature by wire, radio, optical fiber, satellite or other electromagnetic systems or any other service designated as telecom service by the Ministry; and may not include broadcasting service and intercom connection;

2/ ‘‘telecom equipment” means any apparatus used or intended to be used for telecom service, and includes its accessory and software;

3/ ‘‘call-back service” means the use of dial tone of a foreign telecom operator for international connection without the knowledge of the domestic telecom operator or fraudulently making international calls in to apparent domestic calls and shall include services that are identified as call-back by the International Telecommunication Union;

4/ ‘‘Ministry” means the Ministry of Communication and Information Technology;

5/ ‘‘telecom service provider” means the Ethio-Telecom or any other person authorized to provide telecom service;

6/ ‘‘police” means the Federal Police or, as the case may be, regional state police;

7/ ‘‘regional state” means any state referred to in Article 47 (1) of the Constitutional of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

፰/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፱/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀሎች

**፫. ከቴሌኮም መሳሪያዎች ጋር የተያያዙ ወንጀሎች**

፩/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጪ ማንኛውም አይነት የቴሌኮም መሳሪያ የሚያመርት፣ የሚገጣጥም፣ ከውጭ ሃገር የሚያስመጣ ወይም የሚሸጥ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ፲ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር ፩፻ሺ እስከ ብር ፩፻፶ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጪ ማንኛውም አይነት የቴሌኮም መሳሪያ የሚጠቀም ወይም ይዞ የሚገኝ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ፩ እስከ ፬ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር ፲ሺ እስከ ብር ፵ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ያለፈቃድ ሊመረቱ፣ ሊገጣጠሙ፣ ከውጭ ሀገር ሊገቡ፣ ሊሸጡ ወይም ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የቴሌኮም መሳሪያዎችን ዝርዝር እና ቴክኒካዊ ስታንዳርድ ያወጣል፡፡

**፬. የቴሌኮም አገልግሎት ከመስጠት ጋር የተያያዙ ወንጀሎች**

አግባብ ባላቸው ህጎች መሰረት የተሰጠ የፀና ፈቃድ ሳይኖረው የቴሌኮም አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሠማራ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ፯ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ያለፈቃድ በሚሠራበት ጊዜ ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ገቢ ሦስት እጥፍ የሚሆን መቀጮ ይቀጣል፡፡

**፭. ከጠለፋና ተደራሽነት ጋር የተያያዙ ወንጀሎች**

ማንኛውም ሰው ከአገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ ወይም ህጋዊ ተጠቃሚው ወይም ሌላ ስልጣን ካለው አካል ፈቃድ ውጪ፡-

፩/ ማንኛውንም የቴሌኮም ኔትዎርክ፣ አገልግሎት ወይም ስርዓት እንዲቋረጥ ያደረገ ወይም ጣልቃ የገባ እንደሆነ፤

8/ ‘‘person” means a physical or juridical person;

9/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO

## TELECOM FRAUD OFFENCES

**3. Offences Related to Telecom Equipments**

1/ Without prejudice to the provision of sub-article (3) of this Article, whosoever manufactures, assembles, imports or offers for sale any telecom equipment without obtaining prior permit from the Ministry commits an offence and shall be punishable with rigorous imprisonment from 10 to 15 years and with fine from Birr 100,000 to Birr 150,000.

2/ Without prejudice to the provision of sub-article (3) of this Article, whosoever uses or holds any telecom equipment without obtaining prior permit from the Ministry commits an offence and shall be punishable with rigorous imprisonment from 1 to 4 years and with fine from Birr 10,000 to Birr 40,000.

3/ The Ministry shall, in consultation with concerned bodies, prescribe types of telecom equipment the manufacturing, assembling, importation, sale or the use of which may not require permits, and set their technical standards.

**4. Offences Related to the Provision of Telecom Service**

Whosoever provides telecom service without having a valid license issued in accordance with the appropriate laws commits an offence and shall be punishable with rigorous imprisonment from 7 to 15 years and with fine equal to three times the revenue estimated to have been earned by the person during the period of time he provided the service.

**5. Offences Related to Interception and Access**

Whosoever without the authorization of the service provider or lawful user, or any other competent authority:

1/ obstructs or interferes with any telecom network, service or system;

፪/ ማንኛውንም የቴሌኮም ስርዓት የጠለፈ ወይም በማንኛውም ሕገወጥ መንገድ ተደራሽነትን ያገኘ እንደሆነ፤ ወይም

፫/ የቴሌኮም አገልግሎት ደንበኞችን የስልክ ጥሪዎች፣ ዳታዎች፣ መለያ ኮዶች ወይም ሌሎች የግል መረጃዎች የጠለፈ፣ የቀየረ፣ ያበላሸ ወይም ጉዳት ያደረሰባቸው እንደሆነ፤

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ፲ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር ፩፻ሺ እስከ ብር ፩፻፶ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ፮. <u>የቴሌኮም አገልግሎትን ለህገ ወጥ ዓላማ ስለማዋል</u>

ማንኛውም ሰው፡-

፩/ በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፪/፪ሺ፩ ከሚያስቀጣ ወንጀል ጋር የተያያዘ ሽብር የሚያስከትል መልዕክት ለማሰራጨት ወይም በወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ አስነዋሪ የሆነ መልዕክት ለማሰራጨት ማንኛውንም የቴሌኮም ኔትዎርክ ወይም መሳሪያ የተጠቀመ ወይም በጥቅም ላይ እንዲውል ያስደረገ እንደሆነ፤ ወይም

፪/ የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ የሚሰጠውን አገልግሎት ወይም የቴሌኮም መሰረተ ልማትን ለሕገ ወጥ ዓላማ ያዋለ ወይም እንዲውል ያስደረገ እንደሆነ፤

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ፫ እስከ ፰ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር ፴ሺ እስከ ብር ፹ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ፯. <u>የአገልግሎት ዋጋ የማጭበርበር ወንጀል</u>

ማንኛውም ሰው፡-

፩/ ላገኘው የቴሌኮም አገልግሎት መክፈል የሚገባውን ትክክለኛ ዋጋ በተጭበረበረ መንገድ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ፤ ወይም

፪/ ለቴሌኮም አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ መክፈል የሚገባውን የአገልግሎት ዋጋ በተጭበረበረ መንገድ በሌላ ሰው እንዲፈፀምለት በማድረግ የቴሌኮም አገልግሎት ያገኘ እንደሆነ፣ ወይም

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ፭ እስከ ፲ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ተጭበርብሯል ተብሎ የሚገመተውን የቴሌኮም አገልግሎት ዋጋ ሦስት እጥፍ የሆነ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2/ intercepts or illegally obtains access to any telecom system: or

3/ intercepts, alters, destroys or otherwise damages the contents of telephone calls, data, identification code or any other personal information of subscribers;

commits an offence and shall be punishable with rigorous imprisonment from 10 to 15 years and with fine from Birr 100,000 to Birr 150,000.

## 6. <u>UsingTelecom Service for Illegal Purpose</u>

Whosoever:

1/ uses or causes the use of any telecom network or apparatus to disseminate any terrorizing message connected with a crime punishable under the Anti-Terrorism Proclamation No. 652/2009, or obscene message punishable under the Criminal Code; or

2/ uses or causes the use of the telecom service or infrastructure provided by the telecom service provider for illegal purpose;

commits an offence and shall be punishable with rigorous imprisonment from 3 to 8 years and with fine from Birr 30,000 to Birr 80,000.

## 7. <u>Offence Related to Fraud of Service Charge</u>

Whosoever:

1/ fraudulently obtains telecom service without payment of a lawful charge thereof; or

2/ obtains telecom service by means of fraudulent payment charged to another person;

commits an offence and shall be punishable with rigorous imprisonment from 5 to 10 years and with fine equal to three times the charge estimated to have been avoided by the act.

**፰. <u>የኮልባክ አገልግሎትን ስለሚመለከቱ ወንጀሎች</u>**

፩/ ማንኛውም ሰው የኮልባክ አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ፭ እስከ ፲ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና የኮልባክ አገልግሎቱን በሰጠበት ጊዜ ውስጥ ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ገቢ አምስት እጥፍ የሚሆን መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት የኮልባክ አገልግሎት ያገኘ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ፫ ወር እስከ ፪ ዓመት በሚደርስ እስራት እና ከብር ፪ሺ፭፻ እስከ ብር ፳ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

**፱. <u>ህገወጥ የቴሌኮም ኦፕሬተርን ስለሚመለከቱ ወንጀሎች</u>**

፩/ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ ከዘረጋው የቴሌኮም መሰረተ ልማት ውጪ ማንኛውንም የቴሌኮም መሰረተ ልማት የዘረጋ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ የዘረጋውን የቴሌኮም መሰረተ ልማት ወደ ጐን ትቶ የሀገር ውስጥም ሆነ ዓለም አቀፍ የቴሌኮም አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ፤

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ፲ እስከ ፳ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና አገልግሎቱን በሰጠበት ጊዜ ውስጥ ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ገቢ አስር እጥፍ የሚሆን መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ከተመለከተው ህገ ወጥ የቴሌኮም ኦፕሬተር የቴሌኮም አገልግሎት ያገኘ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ፫ ወር እስከ ፪ ዓመት በሚደርስ እስራት እና ከብር ፪ሺ፭፻ እስከ ብር ፳ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

**፲. <u>ሌሎች ወንጀሎች</u>**

፩/ በሕገ ወጥ መንገድ ሲም ካርድ፣ ክሬዲት ካርድ፣ የደንበኞችን መለያ ቁጥር ወይም ዳታ የሚሰራ ወይም የሚያባዛ ወይም በሕገ ወጥ መንገድ የተባዙትን ሲም ካርዶች፣ የደንበኞች መለያ ቁጥሮች ወይም ዳታዎች የሚሸጥ ወይም በማናቸውም መንገድ የሚያሰራጭ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ፲ እስከ ፲፭ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር ፩፻ሺ እስከ ብር ፩፻፶ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

**8. <u>Offences Related to Call-Back Service</u>**

1/ Whosoever provides call-back service commits an offence and shall be punishable with rigorous imprisonment from 5 to 10 years and with fine equal to five times the revenue estimated to have been earned by the person during the period of time he provided the call-back service.

2/ Whosoever intentionally or by negligence obtains any call-back service shall be punishable with imprisonment from 3 months to 2 years and with fine from Birr 2,500 to Birr 20,000.

**9. <u>Offences Related to Illegal Telecom Operators</u>**

1/ Whosoever:

a) establishes any telecom infrastructure other than the telecom infrastructure established by the telecom service provider; or

b) bypasses the telecom infrastructure established by the telecom service provider and provides any domestic or international telecom service;

commits an offence and shall be punishable with rigorous imprisonment from 10 to 20 years and with fine equal to ten times the revenue estimated to have been earned by him during the period of time he provided the service.

2/ Whosoever intentionally or by negligence obtains any telecom service from an illegal operator stipulated under sub-article (1) of this Article commits an offence and shall be punishable with imprisonment from 3 months to 2 years and with fine from Birr 2,500 to Birr 20,000.

**10. <u>Other Offences</u>**

1/ Whosoever illegally manipulates or duplicates SIM cards, credit cards, subscriber identification numbers or data or sales or otherwise distributes illegally duplicated SIM cards, credit cards, subscriber identification numbers or data commits an offence and shall be punishable with rigorous imprisonment from 10 to 15 years and with fine from Birr 100,000 to Birr 150,000.

፪/ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ ማንኛውንም አይነት መሳሪያ ከህዝብ ቴሌፎን ጋር በማገናኘት ወይም ማንኛውንም ሌላ መንገድ በመጠቀም በህዝብ ቴሌፎን አማካኝነት በመደበኛ ሁኔታ ሊገኝ የማይችልን አገልግሎት ያገኘ እንደሆነ፤ ወይም

ለ/ የተሳሳተ ወይም የተጭበረበረ የደንበኝነት ስምምነት በማቅረብ፣ የሌላ ሰው የማንነት መለያ ኮድን በመጠቀም ወይም በሌላ ማንኛውም የተጭበረበረ መንገድ የቴሌኮም አገልግሎት ተጠቃሚ የሆነ ወይም ሌሎች እንዲጠቀሙ ያደረገ እንደሆነ፤

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ፫ እስከ ፰ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር ፴ሺ እስከ ብር ፹ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፫/ ኢንተርኔትን በመጠቀም የስልክ ጥሪ ወይም የፋክስ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ፫ እስከ ፰ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ገቢ አምስት እጥፍ የሚሆን መቀጮ ይቀጣል፡፡

፬/ ማንኛውም ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተውን አገልግሎት ያገኘ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ፫ ወር እስከ ፪ ዓመት በሚደርስ እስራት እና ከብር ፪ሺ፭፻ እስከ ብር ፳ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ፲፩. <u>በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል የሚፈፀም ወንጀል</u>

በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ የሚፈፀም ማንኛውም ወንጀል በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል የተፈፀመ እንደሆነ ለወንጀሉ የተደነገገው መቀጮ በአስር ተባዝቶ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ፲፪. <u>ንብረት ስለመውረስ</u>

ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ መሰረት በጥፋተኛ ላይ ቅጣት ሲወስን ወንጀሉን ለመፈጸም በጥቅም ላይ የዋለ ማንኛውም የቴሌኮም መሣሪያ በመንግሥት እንዲወረስ በተጨማሪነት ያዛል፡፡

2/ Whosoever:

a/ by connecting any equipment to a public pay telephone or by using any other means obtains services which are not normally available through the public pay telephone; or

b/ obtains or causes others to obtain telecom service from the telecom service provider by presenting false or forged service agreement or by fraudulently using the identity code of another person or by using any other fraudulent means;

commits an offence and shall be punishable with rigorous imprisonment from 3 to 8 years and with fine from Birr 30,000 to Birr 80,000.

3/ Whosoever provides telephone call or fax services through the internet commits an offence and shall be punishable with rigorous imprisonment from 3 to 8 years and with fine equal to five times the revenue estimated to have been earned by him during the period of time he provided the service.

4/ Whosoever intentionally or by negligence obtains the service stipulated under sub-article (3) of this Article commits an offence and shall be punishable with imprisonment from 3 months to 2 years and with fine from Birr 2,500 to Birr 20,000.

## 11. <u>Offence Committed by Juridical Person</u>

Where any juridical person commits an offence stipulated under this Proclamation, it shall be punishable with a fine the amount of which shall be equal to ten times the fine stipulated for the offence.

## 12. <u>Confiscation of Property</u>

The court, in deciding the penalty of an offender under this Proclamation, shall give additional order for the confiscaton of any telecom equipment used in the perpetration of the offence.

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፫. ቴክኒካል ግብረ ሃይል ስለማቋቋም

የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀልን ለመከላከል፣ ለመመርመርና ለመቆጣጠር ከሚመለከታቸው አካላት የተውጣጣ ብሔራዊ ቴክኒካል ግብረ ሃይል ይቋቋማል፡፡

### ፲፬. በድብቅ የሚደረግ ብርበራ

ፖሊስ የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመ እንደሆነ ወይም ሊፈፀም እንደሚችል በበቂ ምክንያት ያመነ ከሆነ በድብቅ የሚደረግ የብርበራ ማዘዣ ከፍርድ ቤት እንዲሰጠው በፅሁፍ ፈቃድ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

### ፲፭. ተቀባይነት ስለሚኖራቸው ማስረጃዎች

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርዓት ህግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት የሚቀርቡ ሌሎች ማስረጃዎች ተቀባይነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ማስረጃዎች በቴሌኮም ማጭበርበር ጉዳዮች በፍርድ ቤት በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖራቸዋል፡-

፩/ ዲጂታል ወይም የኤሌክትሮኒክስ ማስረጃዎች፤

፪/ በጠለፋ ወይም በክትትል የተገኙ ማስረጃዎች፤ እና

፫/ በውጭ ሀገር የህግ አስከባሪ አካላት በተደረገ ጠለፋ የተገኙ ማስረጃዎች፡፡

### ፲፮. የዳኝነት ሥልጣን

በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀሎች በመጀመሪያ ደረጃ የመዳኘት ሥልጣን የሚኖረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡

### ፲፯. የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፩/ የቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር ፵፱/፲፱፻፹፱ (በአዋጅ ቁጥር ፪፻፹፩/፲፱፻፺፬ እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፳፭ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፫) በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

፪/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማናቸውም ህግ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### ፲፰. ደንብ የማውጣት ስልጣን

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## PART THREE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 13. Establishment of Technical Task Force

In order to prevent, investigate and control telecom fraud offence a national technical task force comprising members drawn from the concerned bodies shall be established.

### 14. Covert Search

Police may request the court in writing for covert search warrant where a telecom fraud offence has been committed or where he has reasonable ground that a telecom fraud is likely to be committed.

### 15. Admissibility of Evidence

Without prejudice to the admissibility of other evidences to be produced in accordance with the Criminal Procedure Code and other relevant laws, the following shall be admissible in court in relation to telecom fraud offences:

1/ digital or electronic evidences;

2/ evidences gathered through interception or surveillance; and

3/ information obtained through interception conducted by foreign law enforcement bodies.

### 16. Jurisdiction

The Federal High Court shall have first instance jurisdiction over telecom fraud offences provided under this Proclamation.

### 17. Repealed and Inapplicable Laws

1/ Sub- article (1), (2) and (3) of Article 25 of the Telecommunication Proclamation No. 49/1996 (as amended by Proclamation No. 281/2002) are hereby repealed.

2/ No law or customarypractices shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for under this Proclamation.

### 18. Power to Issue Regulation

The Council of Ministers may issue regulation necessary for the implementation of this Proclamation.

**፲፱. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**19. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 4th day of September, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**